# የኮሮና ቫይረስ (የኮቪድ-19) በሽታ ምላሽ አሰጣጥን አስመልክቶ የተዘጋጀ መግለጫ

ባለፉት 24 ሰዓት ውስጥ በተደረገው 4950 የላብራቶሪ ምርመራ አንድ መቶ (100) ሰዎች የኮሮና ቫይረስ ተገኝቶባቸዋል። በአጠቃላይ በሀገራችን ቫይረሱ በምርመራ የተገኘባቸው ሰዎች ቁጥር ስምንት መቶ ሰላሳ አንድ (831) ደርሷል። ቫይረሱ በምርመራ የተገኘባቸው ሰዎች 53 ወንድ እና 47 ሴት ሲሆን የዕድሜ ክልላቸው ከ 3 እስከ 70 ዓመት ውስጥ ይገኛል። በዜግነት ዘጠና ዘጠኝ ሰዎች ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ አንድ ሰው የብሩንዲ ዜጋ ነው። ቫይረሱ በምርመራ የተገኘባቸው ዘጠና አራት (94) ሰዎች ከአዲስ አበባ (ሰላሳ አራት በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር የታወቀ ግንኙነት ያላቸው እና ስልሳ ሰዎች የውጭ ሀገር ጉዞ ታሪክ እና በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር የታወቀ ግንኙነት የሌላቸው) ፣ አንድ (1) ሰው ከትግራይ ክልል (የውጭ ሀገር ጉዞ ታሪክ ያለው እና በለይቶ ማቆያ ያለ) ፣ ሁለት (2) ሰዎች ከሶማሊ ክልል (የውጭ ሀገር ጉዞ ታሪክ ያላቸው እና በለይቶ ማቆያ ያሉ) እንዲሁም ሶስት (3) ሰዎች ከኦሮሚያ ክልል (አንድ በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር የታወቀ ግንኙነት ያለው እና ሁለት የውጭ ሀገር ጉዞ ታሪክ እና በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር የታወቀ ግንኙነት የሌላቸው) ናቸው።

የዕለቱ ታማሚዎች የተጋላጭነት ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፦

| **የተጋላጭነት ሁኔታ** | **ቫይረሱ የተገኘባቸው ሰዎች ቁጥር** |
|---|---|
| የውጭ ሀገር ጉዞ ታሪክ ያላቸው | 3 |
| በበሽታው ከተያዘ ሰው ጋር የታወቀ ግንኙነት ያላቸው | 35 |
| የውጭ ሀገር ጉዞ ታሪክ እና በበሽታው ከተያዘ ሰው የታወቅጋር ግንኙነት የሌላቸው | 62 |
| ድምር | 100 |

በተጓዳኝ ህመም ምክንያት ህክምና ላይ የነበሩ የ70 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሴት ለኮሮና ቫይረስ በሽታ በተደረገ ምርመራ ናሙና ከተወሰደ በኋላ የምርመራ ውጤት ሳይደርስ ህይወታቸው አልፏል። በምርምራው ውጤትም ቫይረሱ እንደተገኘባቸው ስለተረጋገጠ በአጠቃላይ በሀገራችን በቫይረሱ ምክንያት ህይወታቸው ያለፈ ሰዎች ቁጥር ሰባት (7) ደርሷል። የጤና ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት በህልፈተ ህይወታቸው የተሰማቸውን ሀዘን እየገለጹ ለቤተሰቦቻቸው መፅናናትን ይመኛል።

በሌላ መልኩ በትላንትናው ዕለት አስር (10) ሰዎች ከአዲስ አበባ ከበሽታው ያገገሙ ሲሆን በአጠቃላይ በሀገራችን ከበሽታው ያገገሙ ሰዎች ቁጥር አንድ መቶ ዘጠና አንድ (191) ነው።

የጤና ሚኒስቴር፣ ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH, ETHIOPIA

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
Ethiopian Public Health Institute

## በሀገራችን የኮሮና ቫይረስ የሁኔታ መግለጫ

| | |
|---|---|
| አጠቃላይ የተከናወነ የላብራቶሪ ምርመራ | 96,566 |
| በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ የተከናወነ የላብራቶሪ ምርመራ | 4950 |
| በዛሬው ዕለት በበሽታ መያዛቸው በላብራቶሪ የተረጋገጠ | 100 |
| በአጠቃላይ በቫይረሱ ተይዘው በለይቶ ከህክምና ውስጥ ያሉ | 631 |
| በፅኑ ህክምና ላይ ያሉ | 1 |
| አዲስ ያገገሙ | 10 |
| በአጠቃላይ ያገገሙ | 191 |
| በበሽታው ሕይወታቸው ያለፈ | 7 |
| ወደ ሀገራቸው የተመለሱ | 2 |
| እስከ አሁን ድረስ በበሽታው የተያዙ ሰዎች ቁጥር | 831 |

የላብራቶሪ ምርመራ ናሙናዎች ከተለያዩ ይበልጥ ተጋላጭ ከሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች፣ ከጤና ተቋማት፣ በቫይረሱ ከተያዘ ሰው ጋር የቅርብ ንክኪ ካላቸው ሰዎች እንዲሁም በአስገዳጅ ለይቶ ማቆያ ውስጥ ካሉ ሰዎች ተወስዶ የተከናወነ ነው።

የጤና ሚኒስቴርና የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የኮሮና ቫይረስ ሥርጭት መጨመርን ከግንዛቤ በማስገባት ሕብረተሰቡ ጥንቃቄዎችን አዘውትሮ እንዲተገብር ያሳስባሉ። በበሽታው መያዛችን ዕለት-ተዕለት በምናደርገው እያንዳንዱ እንቅስቃሴ የሚወሰን መሆኑን በማስታወስ የኮሮና ቫይረስ መከላከያ አራቱን የ"መ" ህጎች ተግባራዊ በማድረግ የበሽታውን ስርጭት እንድንከላከል በጥብቅ እናሳስባለን።

- **መራራቅ:** አካላዊ ርቀት መጠበቅ፣
- **መታጠብ:** እጅን በተደጋጋሚ በውሃና በሳሙና መታጠብ፣
- **መቆየት:** አስገድጅ ካልሆነ ቤት ውስጥ መቆየት እንዲሁም
- **መሸፈን:** ከቤታችን ወጥተን ስንቀሳቀስ የአፍንና የአፍንጫ መሸፈኛ (የፊት ማስክ) መጠቀም

በማንኛውም ሰዓት ጥቆማ ለመስጠትና መረጃ ለማግኘት እንዲሁም በቫይረሱ መያዛቸው ከተረጋገጡ ሰዎች ጋር የቅርብ ንክኪ ያላቸው ግለሰቦች ሪፖርት ለማድረግ በነፃ የስልክ መስመር 8335 ወይም በ952 ወይም በመደበኛ የስልክ ቁጥር 0118276796 በመደወል ወይም በኢሜል አድራሻችን ephieoc@gmail.com በመጠቀም ወይም ባሉበት ክልል በተዘጋጁ ነፃ የስልክ መስመሮች በመደወል ሪፖርት እንዲያደርጉ ወይም በአካባቢው ለሚገኙ ጤና ተቋማት በስልክ እንዲያሳውቁ እንጠይቀለን።

ዶ/ር ሊያ ታደሰ
የጤና ሚኒስትር
ግንቦት 20 ቀን 2012 ዓ.ም